# በአእምሮ ህመም ወቅት ለታካሚዎች ለእገዛና የጥበቃ እርምጃዎች የሚያገለግል የመረጃ መስጫ ቅጽ (PsychKG NRW)

መልካም ቀን ይሁንልዎ (ስም/የአባት ስም):______________________________,

በቅርቡ ወደ ጤንነትዎ እንዲመለሱ ልንረዳዎ ዝግጁ ነን።

በዚህ በራሪ ጽሁፍ እጅግ ጠቃሚ ስለሆኑ መብቶችና ግዴታዎች ልንገልጽልዎ እንወዳለን። የህጉን ያላጠረ ጽሁፍ በታካሚ ክፍሉ ውስጥ ማየት ይቻላል።

## የአገልግሎቶች ምክንያት

**አጭር መረጃ (ለመረዳት ቀላል)**

ወደ ሆስፒታል እንዲመጡ የተደረጉት በመታመምዎ እና በባህሪዎ የተነሳ በእርስዎና በሌሎች ሰዎች ላይ ከባድ አደጋ በመፈጠሩ ምክንያት ነው።

ይህ እንዲደረግ የሚፈቅደው ህግ ለአእምሮ ህመም አገዛና የመከላከያ እርምጃዎች መውሰጃ ህግ ተብሎ ይታወቃል። ህጉ በማሳጠር ሲጻፍ "PsychKG NRW" ነው።

## የዳኝነት ውሳኔ (§ 14 PsychKG NRW)

**አጭር መረጃ (ለመረዳት ቀላል)**

በሆስፒታል ውስጥ መቆየት አለመቆየት ያለብዎ ስለመሆኑ ዳኛ ይወስናል።

ዳኛው ስለ ህመምዎ በተመለከተ እርስዎን ለማነጋገር ዛሬ ወይም ነገ ይመጣል። ለዳኛው ስለ ሁሉም ነገር ሲነግሩት ይችላሉ። ጠበቃ የማግኘት መብት አሉዎ።

ዳኛው የማይመጣ ከሆነ ይለቀቃሉ። አካሚ ዶክተርዎ አዲስ የPsychKG ስነ ስርዐት ካላዘዘልዎ በስተቀር።

በዳኛው ውሳኔ ላይ በሁለት ሳምንታት ጊዜ ውስጥ ለፍርድ ቤት በጽሁፍ ይግባኝ ማቅረብ ይችላሉ። በሆስፒታል ውስጥ የታካሚ ክፍሉ ሰራተኛ በይግባኝዎ ላይ ድጋፍ ያደርግልዎታል።

## የሰነድ ምዝገባ - የመመርመር መብት(§ 16 PsychKG NRW)

**አጭር መረጃ (ለመረዳት ቀላል)**

ሰራተኛው በህክምናው ወቅት ምን እንዳጋጠመ በተመለከተ ይጽፋል።
ሲሻልዎ በአገዳዎችዎ ላይ ከእርስዎ ጋር በድጋሚ ውይይት ይደረጋል።

ሰራተኛው እርስዎን በተመለከተ የጻፈውን ሁሉንም ነገር ሊያነቡ ይችላሉ።

ይህ የመመርመር መብት ተብሎ ይጠራል።

## ከቤት ውጭ መቆየት (§ 16 para. 1 PsychKG NRW)

**አጭር መረጃ (ለመረዳት ቀላል)**

ታካሚዎች በየዕለቱ ቢያንስ ለአንድ ሰዓት ከቤት ውጭ፣ በአትክልት ቦታ ወይም ቴራንስ ላይ መቆየት ይፈቀድላቸዋል።

## በመግባት ወቅት የሚካሄድ የህክምና ምርመራ (§ 17 PsychKG NRW)

**አጭር መረጃ (ለመረዳት ቀላል)**

በአስቸኳይ በዶክተር ምርመራ ይደረግልዎታል።

ዶክተሩ አሁንም ለእርስዎም ሆነ ለሌሎች ሰዎች አደገኛ ስለመሆን አለመሆንዎ ያረጋግጣል።

## ለሚታመን ሰው የሚሰጥ ማስታወቂያ (§ 17 PsychKG NRW)

**አጭር መረጃ (ለመረዳት ቀላል)**

የሚፈልጉ ከሆነ ለሚያምኑት ሰው (ጓደኞች፣ ቤተሰብ፣ ተንከባካቢ) እርስዎ ሆስፒታል ውስጥ እንደሚገኙ እንነግራለን።

የሚፈልጉ ከሆነም ለህግ ባለሙያ መግለጽ እንችላለን።

ሕጋዊ ተወካይ ካለዎ፣ ለተወካይዎ በፍጥነት ይገለጽለታል።

እነዚህ ሰዎች እርስዎ ከዳኛ/ዋና ዳኛ ጋር በሚያካሂዱት ቃለ መጠይቅ ላይ ሊሳተፉ ይችላሉ።

## ህክምና (§ 18 PsychKG NRW)

## አጭር መረጃ (ለመረዳት ቀላል)

በሽታዎ እኛ ጋር ሊታከም ይችላል። ህክምና የሚደረግልዎት በህክምናው የሚስማሙ ከሆነ ብቻ ነው። ይህ ስምምነት/ፍቃድ ይባላል. ስምምነቱ በተጨማሪም በመድሀኒቶች ላይም ይሰራል። ለዚህ ህግ የተቀመጡ ልዩ ሁኔታዎች አሉ።
በህክምናው ላይ ከእርስዎ ጋር በዝርዝር ውይይት መደረግ አለበት።

1. ልዩ ሁኔታ:
በህመምዎ ምክንያት ከባድ አደጋ የሚፈጠር ከሆነ ዶክተር ያለ ፍቃድዎ ህክምና ሊሰጥዎ ይችላል። ትልቅ አደጋ የሚፈጠረው ከህመምዎ ጋር በተያያዘ ባህሪዎ ምክንያት በእርስዎ ህይወት ላይ አደጋ ሲፈጠር ወይም በእርስዎም ሆነ በሌሎች ሰዎች ላይ እጅግ ከባድ የጤና ስጋቶች ሲፈጠሩ ነው።
እንደ ህግ አስገዳጅ ህክምና ሊካሄድ የሚችለው ለህክምናው በዳኛ ፍቃድ ሲሰጥ ብቻ ነው።

2. ልዩ ሁኔታ:
በጣም በጥቂት አጋጣሚዎች ዶክተር በተጨማሪም ዳኛ ሳይጠይቅ ህክምና ሊሰጥ ይችላል። ይህ ዶክተሩ ዳኛ እስከሚደርስ ድረስ መጠበቅ እንደማይቻል - ያለበለዚያ ግን መጥፎ ነገር ያጋጥማል ብሎ ሲያስብ ነው።
እነዚህ ሁለት ልሐዩ ሁኔታዎች አስገዳጅ ህክምና. ተብለው ይጠራሉ።

## ልዩ የደህንነት እርምጃዎች (§ 20 PsychKG NRW)

### አጭር መረጃ (ለመረዳት ቀላል)

እርስዎ ለራስዎም ሆነ ለሌሎች ሰዎች በታወቀ ሁኔታ አደጋ ከሆኑ ዶክተሩ የሚከተሉትን እርምጃዎች ሊያዝ ይችላል:

1) ወደ ውጭ መውጣት እንደሌለብዎ፣

ወይም

2) ለብቻዎ ወደሚሆኑበት ክፍል ተወስደው በዶክተር እንዲቆለፍብዎ።

ወይም

3) ሰራተኛው በእስር ሊያቆይዎ ይችላል።

ወይም

4) ሰራተኛው ከአልጋ ጋር ሊያስርዎ ይችላል።

እነዚህ እርምጃዎች የሚፈቀዱት ከእነዚህ ውጭ ሊረዳ የሚችል ነገር ከሌለ ብቻ ነው። እርምጃዎቹ ከዚህ በኋላ የትኛውም አደጋ የማይፈጠር ከሆነ ወዲያውኑ እንዲቆሙ መደረግ አለባቸው።

ከ30 ደቂቃዎች በላይ እገዳ ከተጣለብዎ ይህ በዳኛ/ዋና ዳኛ መፈቀድ አለበት።

ሲሻልዎ ዳኛን በጥብቅ መታሰር ያለብዎ ስለመሆኑ እንዲያረጋግጥ ሊጠይቁ ይችላሉ።

## የአገልግሎት መቋረጥ (§ 15 PsychKG und § 25 PsychKG)

### አጭር መረጃ (ለመረዳት ቀላል)

አገልግሎቶቹ አሁንም የሚያስፈልጉ ስለመሆኑ ለማወቅ በየዕለቱ ማረጋገጫዎች መደረግ አለበት።

የመሻል ስሜት ሲሰማዎ የሚከተሉትን ማድረግ ይችላሉ:

- እረፍት ማግኘት ወይም
- መሰናበት/መለቀቅ ወይም
- በፍቃደኝነት ህክምናውን መውሰድዎን መቀጠል።

## የግል ንብረቶች፣ ጠያቂ፣ ረተሌኮሙኒኬሽንና ሚዲያ፣ ሲጃራ ማጤስ (§ 22 PsychKG)

### አጭር መረጃ (ለመረዳት ቀላል)

አደገኛ ቁሶች ነርስ ጋር እንዲቀመጡ መደረግ አለበት። ቁሶቹ በሚወጡበት ወቅት ይመለሱልዎታል።

የሞባይል ስልክዎን እና ላፕቶፕዎን ሊጠቀሙ ይችላሉ። እንዲሁም ደብዳቤዎች ሊልኩ ይችላሉ። ደብዳቤዎች መቀበልም ይፈቀድልዎታል። በተጨማሪም ፍላጎትዎ ከሆነ ጠያቂ ሊጠይቅዎ ይችላል።

እባክዎ በታካሚ ክፍሉ ውስጥ ለሚገኙት ለሌሎች ታካሚዎች ያስቡ።

ለማጤስ በተፈቀደው ቦታ ብቻ ሲጃራ ሊያጤሱ ይችላሉ። ቦታው ቀደም ብሎ ምልክት የተደረገበት ነው።

በLVR ክሊኒክ ውስጥ ፍቃድ ሳይሰጥዎ ሌሎች ሰዎችን ፎቶ ማንሳት ወይም በድምጽ መቅረጽ አይፈቀድልዎትም።

## የህክምና ወጪዎች

### አጭር መረጃ (ለመረዳት ቀላል)

የጤና መድን ዋስትና ከሌሉዎ ይህን ያሳውቁን። የLVR ክሊኒኩ ማህበራዊ አገልግሎቶች በዚህ ላይ ይረዱዎታል።

## የህክምና ስምምነት፣ በህይወት የሚሰጥ ኑዛዜ (§ 2 PsychKG NRW)

### አጭር መረጃ (ለመረዳት ቀላል)

ከተወሰነ ጊዜ በኋላ በእኛ በድጋሚ ህክምና ሊደረግልዎ ይችላል።

በዚህ ጊዜ እንዴት በተሻለ ሁኔታ ልናክምዎ እንደምንችል ለማወቅ ያስችለን ዘንድ ከዶክተርዎ ጋር የጽሁፍ ስምምነት ሊያደርጉ ይችላሉ። ይህ የህክምና ስምምነት ተብሎ ይጠራል።

በተጨማሪም የታካሚ ቅድመ መመሪያን እናከብራለን።

ይህ ስምምነት በቀጣይ በሁሉም ተሳታፊ ታካሚዎች ላይ ተግባራዊ ይደረጋል።

## ቅሬታዎች (§ 24 PsychKG NRW)

### አጭር መረጃ (ለመረዳት ቀላል)

እርካታ ካልተሰማዎ ቅሬታ ማቅረብ ይችላሉ።

ቅሬታዎችን በተለያዩ መንገዶች ሊያቀርቡ ይችላሉ። ጠቅላላ ሀሳቡ በታካሚ ክፍል ውስጥ ይለጠፋል። ወይም ሰራተኞችን ሊጠይቁ ይችላሉ።

ቅሬታ የሚቀርብባቸው ሌሎች ዘዴዎች አሉ (ለአድራሻዎች አባሪውን ይመልከቱ):

**በፍጥነት እንዲያገግሙ እንመኝልዎታለን!**
**የLVR ክሊኒክዎ**

## አባሪ:

## ቅሬታ ማቅረቢያ አማራጮች

ሁልጊዜም ይግባኝ የማለት አማራጭ አሉዎት፣ ለምሳሌ: ስለ ህክምናዎ ወይም ስለ ሌሎች ነገሮች በተመለከተ።

**1. የታካሚ ክፍሉ የሳይት ሰራተኞች:**
የነርስ አገልግሎት፣ የነርስ ክፍል ወይም የመምሪያ አስተዳደር ሰራተኞችን፣ ወይም ከፈለጉ ዶክተሮችን ያነጋግሩ *።

ወይም:

**2. እምባ ጠባቂዎች ተብለው የሚጠሩት የክሊኒኩ የሳይት ገለልተኛ የታካሚ ጠበቆች:**
ታካሚዎችን ለመርዳት በLVR ክሊኒክ ውስጥ ለእርስዎ ጊዜ የሚሰጡና የሳይት ላይ ስጋቶችዎን ሊያወያዩዋቸው የሚችሏው ገለልተኛ እምባ ጠባቂዎች ይመደባሉ። የእምባ ጠባቂው የአገልግሎት ሰዓት እና የስልክ ቁጥርን ከሳይት የታካሚ ክፍል የማስታወቂያ ቦርድ ላይ ማግኘት ይችላሉ።

ወይም:

**3. በተጨማሪም በሳይት ላይ የLVR ክሊኒክን የህክምና ዳይሬክቶሬት ማግኘት የሚችሉ ሲሆን ዳይሬክቶሬቱ በደስተኝነት በቀጥሮ ያነጋፍርዎታል:**
የታካሚ ክፍሉ ሰራተኞች ቀጠሮ በማስያዝ ላይ ሊያግዙዎ ዝግጁ ናቸው።

የLVR ክሊኒክ የህክምና ዳይሬክቶሬት የግንኙነት/አድራሻ ዝርዝሮች:

ወይም:

**4. ከLVR ክሊኒክ ውጭ ቅሬታዎን ይዘው ሊቀርቡ ይችላሉ:**
የ Landschaftsverbandes Rheinland ማዕከላዊ የቅሬታ አስተዳደር

Landschaftsverband Rheinland/ ZBM
50663 Köln/ኮሎኝ
ስልክ: 0221/ 809 2255, E-Mail: beschwerden@lvr.de

ወይም:

**5. በመጨረሻም በተለያዩ ቦታዎች ለሚገኙ የአእምሮ ታካሚዎች ገለልተኛ የምክር አገልግሎት ማዕከላትን ያነጋግሩ፤ ለምሳሌ፡**

### ለኮሎኝ ክልል

የኮሎኝ የቅሬታዎች ካውንስል የማህበራዊ ስነ ልቡና የስራ ቡድን/Beschwerderat Psychosoziale Arbeitsgemeinschaft (PSAG) Köln
c/o Rat und Tat e.V. Kempener Str. 135, 50733 Köln,
ስልክ: 0163/ 383 1686፣ኢሜይል: beschwerderat@web.de

### ለዱስልዶርፍ ክልል

የዱስልዶርፍ ገለልተኛ የቅሬታዎች ሰሚ ቢሮ የማህበራዊ ስነ ልቡና የስራ ቡድን/ Unabhängige Beschwerdestelle Psychosoziale Arbeitsgemeinschaft (PSAK) Düsseldorf
Kölner Str. 180, 40227 Düsseldorf
ስልክ: 0211/ 899 2622 የጥሪ መቀበያ ማሽን፣
ኢሜይል: psag_beschwerdestelle@duesseldorf.de

### የዱይስቦርግ ኢሴን ክልል

የዱይስቦርግ ገለልተኛ የቅሬታዎች ሰሚ ቢሮ የማህበራዊ ስነ ልቡና የስራ ቡድን/ Unabhängige Beschwerdestelle der Psychosozialen Arbeitsgemeinschaft (PSAG) Duisburg
በህዝብ ጤና ቢሮ በሚ/ር Marcel Hellmich,
Ruhrorter Straße 195, 47119 Duisburg በኩል
ስልክ: 0203/ 283 2709፣ኢሜይል: beschwerdestelledu@gmx.de

### የክሬፌልድ ክልል

የክሬፌልድ የማህበራዊ ስነ ልቡና ቅሬታዎች ሰሚ ቢሮ/ Psychosoziale Beschwerdestelle Krefeld
Westwall 134, 47798 Krefeld
ስልክ: 02151/ 389 261 የጥሪ መቀበያ ማሽን፣ ኢሜይል: beschwerdestelle@psag-krefeld.de

**የViersen ክልል**

የ Kreis Viersen የማህበረሰብ የአእምሮ ህክምና ማህበር የቅሬታ ሰሚ ቢሮ/
Beschwerdestelle des Gemeindepsychiatrischen Verbundes Kreis Viersen
የግንኙነት መረጃ: BIS e.V., Klosterstr 5, 41379 Brüggen
ስልክ: 02163/ 5622፣ኢሜይል: info@bis-brueggen.de

ወይም:

**6. ችግሮችዎ በበቂ ሁኔታ እንዳልተፈቱ ከተሰማዎ በPsychKG ክፍል 30 መሰረት ለተቆጣጣሪ ዲስትሪክቱ አስተዳደር ቅሬታዎን የሚያቀርቡበት አማራጭ አሉዎ:**

- Bezirksregierung Köln, Krankenhausaufsicht, Postfach, 50606 Köln
- Bezirksregierung Düsseldorf, Krankenhausaufsicht, Postfach 300865, 40408 Düsseldorf

**ዕትም:**
2ኛ ዕትም፣ ጥቅምት 2022 ዓ.ም
ለይዘት ኃላፊነት የተሰጠው:
የLVR መምሪያ 8/ 84.20 ከ81.30 (የህግ መምሪያ) ጋር በመተባበር የግንኙነት ባለሙያ: Uwe Blücher 84.20.

**አስተዋጽኦ አድራጊዎች:**
የሶስቲዮሽ አርትኦት በ: ለዚህ በራሪ ጽሁፍ ተስማሚ ዝግጅት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደረጉት የLVR clinics የማገገሚያ ድጋፍ ሰራተኞች፣ የዘመድ ተወካዮች፣ የአእምሮ ሀኪምና ሳይኮቴራፒስት፣ የነርሲንግ መምሪያ ኃላፊ፣ የህዝብ ግንኙነት ኦፊሰር፣ የSEIB የንዑስ ፕሮጀክት አስተዳደር፣ የውህደት ኦፊሰር፣ ZBM፣ የLVR ክሊኒኮች የነርሲንግ ዳይሬክቶሬቶችና የህክምና ዳይሬክቶሬቶች።
የዚህ በራሪ ጽሁፍ ተግባራዊነት አስተዋጽኦ።

**የጽሁፍ አቀራረብ:** በቀላል ቋንቋ ህጎች (Verein Netzwerk Leichte Sprache e.V.) እንዲሁም በLVR መምሪያ 1 የሰርኩላር ትእዛዝ ቁ. 2 ላይ ተመስርቶ ለመረዳት ቀላል በሆነ ቋንቋ (ዜጎችን ማዕከል ያደረገ)።

**የቋንቋ ቅጂዎች:**
የPsychKG በራሪ ጽሁፍ የ32-ቋንቋዎች ትርጉሞችን ያገኛሉ።

የሚከተለውን የቅጂ መብት ማስታወቂያ በማካተት በራሪ ጽሁፉን ወደ ውጭ ማሰራጨት ይቻላል:
© LVR-Klinikverbund እና Verbund Heilpädagogischer Hilfen